# አማሌቅ ይሸነፍ

በመጋቢ አስቻለው በየነ

## ክፍል አንድ

በዚህ በያዝነው ዓመት እ.ኤ.አ. 2007፣ እግዚአብሔር አማሌቅን የምናሸንፍበትን ሃይልና ጉልበት ሊያጎናፅፈን አልፎም የራሱን መለኮታዊ የውጊያ ስልት ሊሰጠን ይፈልጋል:: መንደርደሪያ እንዲሆነን የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ወስደን በመመልከት እግዚአብሔር ሊናገረን የሚፈልገውን መልዕክት እንረዳ::

> *«አማሌቃውያን መጥተው እስራኤላውያንን ራፊዲም ላይ ወጉ ሙሴም ኢያሱን ከሰዎቻችን አንዳንዶቹን ምረጥና አማሌቃውያንን ለመውጋት ውጣ:: በነገው እለት የእግዚአብሔርን (ኤሎሂም) በትር በእጆቼ ይዤ በኮረብታው ጫፍ ላይ እቆማለሁ::ስለዚህ ኢያሱ ሙሴ ባዘዘው መሰረት ከአማሌቃውያን ጋር ተዋጋ ሙሴ አሮንና ሖርም ወደ ኮረብታው ጫፍ ወጡ:: ሙሴ እጆቹን ወደ ላይ በሚያነሳበት ጊዜ ሁሉ እስራኤላውያን ድል ያደርጉ ነበር:: እጆቹን ባወረደ ጊዜ አማሌቃውያን ያሸንፉ ነበር:: የሙሴ እጆች እየዛሉ በሄዱ ጊዜ ድንጋይ ወስደው ከበታቹ አደረጉ እርሱም ተቀመጠበት አሮንና ሖርም አንዱ በአንዱ በኩል ሌላው በሌላ በኩል ሆነው እጆቹን ወደ ላይ ያዙ:: ይኸውም እጆቹ ፀሐይ እስክትጠልቅ ድረስ ጸንተው እንዲቆዩ ነው:: ስለዚህ ኢያሱ የአማሌቃውያንን ሰራዊት በሰይፍ ድል አደረገ:: ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን «ሲታወስ እንዲኖር ይህን በጥቅልል መጽሐፍ ላይ ጻፈው ኢያሱም መስማቱን አረጋግጥ ምክንያቱም የአማሌቃውያንን ዝክር ከሰማይ በታች ፈፅሜ እደመስሳለሁ»አለው::ሙሴም መሠዊያውን ሰርቶ «እግዚአብሔር (ያህዌ) አርማዬ ነው» ብሎ ሰየመው:: «እጆች ወደ እግዚአብሔር (ያህዌ) ዙፋን ተዘርግተዋልና እግዚአብሔር (ያህዌ) አማሌቃውያንን ከትውልድ እስከ ትውልድ ይዋጋቸዋል» አለ::*
> **ዘዳ.17÷8-15**

### 1) ውጊያው መንፈሳዊ እንጂ ሥጋዊ አይደለም!

የዚህ ነገር ቁልፍ ምስጢር ያልገባው አማኝ በዚህ ምድር ላይ የድልን ሕይወት ለመኖር አይችልም:: ስለዚህ ጠላት ይህንን ስለሚያውቅ የብዙ ክርስቲያኖችን የጸሎት ሕይወት የቀማው በተለያዩ ነገሮች ተጠምደው እንዲባክኑ በማድረግ ነው! ቀደም ብለን ባነበብነው ክፍል ውስጥ የምንገነዘበው ነገር እስራኤል ባለ ድል የሆነው ኢያሱ ስለተዋጋ ብቻ ሳይሆን ሙሴም በተራራ ላይ ሆኖ እጆቹን ወደ እግዚአብሔር ስላነሳ ነበር::

የሙሴ እጆች ሲበረቱ ኢያሱ ይበረታል የሙሴ እጆች ሲደክሙ ደግሞ የኢያሱም ይደክማል ስለዚህ የሙሴ እጆች ወደ ላይ ካልተነሱና ካልበረቱ የኢያሱ እጆች ብቻቸውን ምንም ማድረግ አይችሉም ማለት ነው:: ሙሴና ኢያሱ አንድ ቦታ ላይ ቆመው አልተዋጉም ምንም እንኳ በሚታይ ቦታ የቆመው ኢያሱ ቢሆንም ወይም በዓይን ከሚታይ ጠላት ጋር የተዋጋውና የተጋፈጠው ኢያሱ ቢሆንም የሙሴ ሥፍራ ግን በጠላት ፊት ሳይሆን በእግዚአብሔር ፊት ነበር:: ድል ለእስራኤል የመጣው በእግዚአብሔር ፊት ከቆመው ከሙሴ እንጂ በጠላት ፊት ከቆመው ከኢያሱ አልነበረም::

ስለሆነም የዚህ ነገር ምስጢር ከገባን ቶሎ ብለን ወደ ትክክለኛው ስፍራችን መመለስ ይኖርብናል ምክንያቱም ወደ ተራራው ስንወጣ ወይንም ወደ ፀሎት ሥፍራ ስንመለስ ጠላት ይሸነፋል:: ድል ያለው በተራራ ላይ እንጂ በሜዳ ላይ አይደለምና!

> ***ወደ ተራራው ስንወጣ ወይንም ወደ ፀሎት ሥፍራ ስንመለስ ጠላት ይሸነፋል:: ድል ያለው በተራራ ላይ እንጂ በሜዳ ላይ አይደለምና!***

### 2) የእግዚአብሔር በትር

ሙሴ ወደ ተራራው በወጣ ጊዜ ባዶ እጁን ሳይሆን የእግዚአብሔርን በትር ይዞ ነበር የወጣው:: የእግዚአብሔር በትር ሲል ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ነገር ይዞ መውጣቱን ያሳያል:: አማኝ የሚዋጋው የእግዚአብሔርን ነገር ይዞ እንጂ የራሱን ነገር ይዞ አይደለም:: ጠላታችንንም የምናሸንፈው በእግዚአብሔር ነገር እንጂ በሰው ነገር አይደለም::